# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

***መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም.***

**የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ለሁለት ቀናት ሳይናገሩ ዋሉ፤**

**አዳዲስ ከባድ የጦር መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ገባ፤**

**የወያኔ የጦር መኮንኖች መሀከል ሽኩቻ ተፈጠረ፤**

የወያኔ ማዕከላዊ ምክር ቤት አባሎች በፍርሀት እና በድንጋጤ ተውጠው በአንድ ሰው ተናጋሪነት ብቻ ለሁለት ቀናት ዝግ ስብሰባ ማድረጋቸው ከስብሰባው ተሳታፊዎች ሾልኮ የወጣው ጥቆማ አጋለጠ።

ለሁለት ቀናት በተደረገው በዚሁ ዝግ ስብሰባ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጥቂት ከሚባሉ ሀሳቦች ያውም የመለስ ቀኝ እጅ ናቸው ከሚባሉት በረከት ስምኦን፣ሬድዋን ሁሴን እና ኃይማርያም ደሳለኝ በስተቀር በአንድ ሰው ብቻ መድረኩ ተይዞ ሁሉም አንገቱን ደፍቶ እንዳሳለፈ የስብሰባው ተሳታፊ ከፍተኛ አመራሮች በምሬት ሲናገሩ እንደነበር ታውቆዋል።

ከጊዜ ወደ ግዜ ......ከቀን ወደ ቀን....... ባህሪው እየተለዋወጠ የመጣው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከወትሮው በበለጠ ሁኔታ የተሰብሳቢ ባለስልጣናቱን ሀሳብ ሳያዳምጥ እራሱ ያዘጋጀውን አውርቶ በሙሉ ድመፅ እንዲያሳልፉለት ከማድረግ ባሻገር ተጨማሪም ሆነ ተለዋጭ ሀሳብ ትንፍሽ እንዳይሉ በማድረግ ብቻውን ጀምሮ ብቻውን የጨረሰበት ስብሰባ ማድረጉ ባለስልጣናቱን ግራ እንዳጋባም ተጠቁሞዋል።

መለስ ዜናዊ እንደ ወፈፌ ብቻውን እያወራ ብቻውን እየሳቀ ባሳለፈው በዚሁ ዝግ ስብሰባ ላይ በረከት ስምኦን የመለስን ሀሳብ ደግፎ ተጨማሪ ማብራሪያ ከመስጠት ያለፈ ሌላ አንድም ባለስልጣን ሳይናገር ከመውጣቱም በተጨማሪ አንዴ ፈገግ ሌላ ግዜ ኩስትር እያለ ባለስልጣናቱን እየገረመመና እያስፈራራ ሲያስጨንቃቸው እንደነበር ያጋለጡት ባለስልጣናቱ በባህሪው መለዋወጥ ክፉኛ እንደደነገጡም  ገልፀዋል።

በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ የተከሰተው የኑሮ ውድነት ህዝቡን  ችግር ውስጥ ከመዝፈቁም በላይ ሊወጣው ከሚችለው አዘቅት ውስጥ እንደከተቱት እያወቁ እና  በገሀድ እየታየ ከፍተኛ የእድገት እመርታ እንደተጀመረ አድርጎ ማቅረቡ...... በነጋዴዎች ላይ መወሰድ የተጀመረው እርምጃ ቀጣይ እንደሚሆን..... በመላከያም በኩል ሊደጎም የታሰበው በጀት ተገቢ መሆኑን ባቀረበው መብራሪያ የገለፀ ቢሆንም ባለስልጣናቱ አንዳችም ሀሳብ ሳይሰጡበት በእጅ ማውጣት ብቻ እንዲፀድቅ ማድረጉ እያነጋገረ መሆኑም ታውቆዋል።

በዘይት አስመጪና አከፋፋይነት ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩትን  ነጋዴዎች የንግድ ፍቃዳቸውን ቀምቶና ሰርዞ ጨርሶ እንዳይላወሱ አድርጎ ባለበት ሰዓት እንደገና በሌሎች የንግድ መስክ በተሰማሩትም ላይ የጥቃት በትር ሊዘረጋ መዘጋጀቱን ተስማምተው ያለ አንዳች ተቃውሞ በሙሉ ድመፅ ያሳለፉት የወያኔ ባለስልጣናት ከስብሰባ በሁዋላ በመለስ ትዕዝዝ እና አስገዳጅነት የተፈጸመ ነው እያሉ ወሬ እያናፈሱ  መገኘታቸው ያሉበትን አሳዛኝ ሁኔታ የሚያስረዳ ነው።

:

ዝግና ምስጢር ነው በተባለለት በዚሁ ስብሰባ ላይ ዋነኛ አጀንዳ ከተባሉት ውስጥ የነጋዴው ስር ነቀል የሆነ እርምጃ መወሰድ  መጀመሩ ተገቢ እንደሆነ......ህዝቡ የኑሮ መሻሻል እየታየ ያለው በወያኔ ጠንካራ አመራር መሆኑን......ከውጭ የሚመጡ ባለሀብቶች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ምቹ ሁኔታ የተፈጠረላቸው መሆኑን .....የሻእቢያ ተቀናቃኞችን በገንዘብም ሆነ በቁሳቁስ መደገፋቸው አግባብ መሆኑን መለስ አቅርቦ በሙሉ ድምፅ እንዲፀድቅ መደረጉን  የስብሰባው ተሳታፊ አኩራፊ ባለስልጣናት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በስብሰባው ላይ ማብራሪያ እየሰጠ ባለበት ወቅት ድንገት ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ አፍኖ በመያዝ ለረዥም ደቂቃዎች እንደሚቆይ ያጋለጡት እነዚሁ ባለስልጣናት  ሰውዬው ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ በመግባቱ የተነሳ ቀድሞ የነበረው የጭንቅላት በሽታ ሳያገረሽበት እንዳልቀረም ተናግረዋል።

በተያያዘ ዜና የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለ20 ዓመታት ብቻውን እንዳሻው ሲጨፍርበት የኖረውን ስልጣን የበለጠ ለማጠናከር ሲል  ከበረሀ የመጡ ጉዋደኞቹን በጡረታ እና በአምባሳደርነት ስም እያገለለ መምጣቱን ለቤተ መንግስት ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገለፁ።

በአሁኑ ሰዓት መለስ በሶስት ባለስልጣናት ብቻ በመታገዝ ሀገሪቱን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ ያለበት ሲሆን እነዚህም በረከት ስምኦን ፣ሬድዋን ሁሴን እና ኃይለማርያም ደሳለኝ ናቸው፡፡

በሌለ ዜና የወያኔ ቡድን አሁንም የጦር መሳሪያ ከቻይና እየገዛ ወደ ሀገር ውስጥ እያስገባ መሆኑ ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ፡፡

በቅርቡ አስቸኩዋይ በሚል ትዕዛዝ ከዓመታዊ በጀት ውጭ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር አዲስ በጀት የተመደበለት የወያኔ መከላከያ መስሪያ ቤት ካለፈው ሳምንት ጀምሮ እስከ ዛሬዋ  እለት ድረስ ቁጥራቸው የበዛ የጭነት መኪኖች በኮንቲነር የታሸጉ የጦር መሳሪያዎች እና ጥይቶቻቸውን እያጉዋጉዋዘ መሆኑን ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

በታሸጉ ኮንቲነሮች ቀላልና መሀከለኛ የጦር መሳሪያዎች ወደ መሀል ሀገር እየተጉዋጉዋዘ ከመሆኑም በተጨማሪ አዲስ ሞዴል ባለ ሰንሰለታማው ታንኮች በሎቤድ እያስጫነ እያስገባ መሆኑ የታየ ሲሆን ሌሎችም ከባድና ቀላል የጦር መሳሪያዎች ወደብ ላይ  እንደደረሱ ከአይን እማኞች የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ባለ ሰንሰለታማው አዲስ ሞዴል ታንኮች በጅቡቲ ወደብ ላይ ሰፍረው ከስር ከስር ወደ መሀል ሀገር እየገቡ ከመሆኑም በተጫማሪ ገሚሶቹ በአዋሽ አርባ ማሰልጠኛ ጦር ከምፕ ውስጥም እየገቡ ሸራ ለብሰው እንዲቀመጡ እየተደረጉ መሆኑን የመከላከያ ምንጮች ጠቁመዋለ፡፡

ህዝቡ በኑሮ ውድነት እግር ከወርች ተጠፍሮ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔ ቡድን የሀገሪቱን ከዝና እየዘረገፈ ለጦር መሳሪያ መግዣ እያዋለው መሆኑ የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ በጎንደርና በትግራይ......በምስራቅ በኩል በደገሀቡር እና ቀላፎ ጎዴ.......በጅቡቲ በኩል አዳይቱ......በደቡብ በኩል ቦረና .......እና በሌሎችም ክልሎች በየግዜው ግዙፍ የጦር  እያጉዋጉዋዘ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በተለይ ሰሜንና በምስራቅ የተፈጠረበት ችግር ምን እንደሆነ ባይታወቅም ከፍተኛ የስጋት አቅጣጫዎቹ በመሆናቸው በክፍለ ጦሮች ደረጃ አስፍሮ እንደሚገኝም የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

በሻእቢያ ሰልጥነው ሀገር ሊያተራምሱ ሲሉ ከነ ሙሉ ትጥቃቸው ተያዙ ተብሎ በወያኔ ሚዲያ በኩል ከተገለፀ ወዲህ በጅቡቲ አዋሳኝ ድንበሮች ላይ በከባድ የጦር መሳሪያ የታገዘ ግዙፍ ጦር መስፈሩን የጠቆሙት ምንጮቹ  ምናልባትም ሻእቢያ ያልታሰበ ጥቃት ሊሰነዝር ይችላል የሚል ስጋት በማሳደሩ ጦሩን ሊያሰፍር እንደቻለ ምንጮቹ ግምታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ ተመሳሳይ ጥቃት ሊሰነዝር ይችላል በሚል ስጋት እና ፍርሀት የተነሳ ሁለት ክፍለ ጦር ሱዳን እና ኢትዮጵያ አዋሳኝ ድንበር ላይ እንዲሰፍር የተደረገ ሲሆን በቅርቡ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ከባድ የጦር መሳሪያዎችም ወደ ድንበር እንደተጠጉላቸው ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ለብዙ ዓመታት በሰራዊቱ ውስጥ በሹፌርነት ሲያገለግሉ የነበሩት የጦሩ አባሎች በሰራዊቱ ውስጥ ባለው መድልኦ በመበሳጨት ስራቸውን በገዛ ፍቃዳቸው በመልቀቃቸው የተነሳ መኪኖችን የሚያንቀሳቅስ በመጥፋቱ በቅርቡ ለ3 ወራት ያሰለጠናቸውን አዲስ ምልምል ሹፌሮች ማስመረቁም ታውቆዋል።

እነዚህ አዲስ ልም ሹፌሮች ራሽያ ሰራሽ የሆኑ ኦራል የተሰኙ የበረሀ መኪኖች ተሰጥዋቸው ጦሩን ከቦታ ወደ ቦታ እያዘዋወሩ ቢሆንም ብዙዎቹ ከችሎታ ማነስ የተነሳ መኪና እየገለበጡ ቁጥራቸው የበዛ ወታደሮች እየሞነ መሆኑን ከመከላከያ ሰው ኃይል ክፍል መምሪያ ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

የሰሜን ኢትዮጵያ የመሬት አቀማመጥ አስቸጋሪ መሆኑና የሹፌሮቹ የልምድ ማጣት ጋር ተዳምሮ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ የሰራዊቱ አባሎች እየሞቱና የአካል ጉዳት እየደረሰባቸው ከመሆኑም በላይ የሀገር ሀብት የሆነው መኪናም እየወደመ በየቀኑ ከፍተኛ ኪሳራ እየደረሰ እንደሚገኝ እነዚሁ የመከላከያ ምንጮች ገልፀዋል።

ነባር መኮንኖችን በተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶች ከሰራዊቱ እያባረረ የሚገኘው የወያኔ ቡድን ይህንኑ ችግር ይቀርፋሉ ተብለው ከበረሀ የመጡ ታጋይ የአሁኖቹ ከፍተኛ መኮንኖች የውጭ ትምህርት እንዲማሩ ከውጭ ሀገር በከፍተኛ ገንዘብ ተቀጥረው ከገቡት መምህራኖች ጋር በቁዋንቁዋ መግባባት ባለመቻላቸው በአማርኛ ቁዋንቁዋ ብቻ እንዲማሩ የተደረገ ሲሆን እነዚሁ ስልጠና ወሰዱ የተባሉት ጄኔራል መኮንኖች ባለፈው ሳምንት መመረቃቸው ታውቆዋል።

በመለስ ዜናዊ የክብር እንግዳነት በቤተ መንግስት ውስጥ በምስጢር የተመረቁት እነዚሁ የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች ወደፊት የመከላከያን ስልጣኖች ሊረከቡ እንደሚችሉ ተስፋ የተሰጣቸው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በአሁኑ ሰዓት በስልጣን ላይ ያሉት ጄኔራሎች ከመስጋታቸው የተነሳ ከአዲሶቹ ተመዳቢ መኮንኖች ጋር መተማመን ጠፍቶ የጎሪጥ እየተያዩ መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል።